# የሲያትል የትራንስፖርት ክፍያ





## የ JUNE 2015 የመረጃ ሰነድ

AMHARIC

### ዳራ

የሲያትል ጎዳናዎች፣ የመንገድ ዳር መረማመጃዎች እና ድልድዮች በየቀኑ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎችን ያጓጓዛሉ፡፡ በተጨማሪም እነዚህ መንገዶች እቃዎች ወደ ከተማዋ እንዲጫኑ በማድረግ መጋዘኖች በእቃ እንድሞሉ እና የሚፈለጉ ዕቃዎች በቤትዎ በር ላይ እንዲያገኙ በማድረግ የጭነት አገልግሎት ያግዛሉ፡፡

ባለፉት ስምንት እና ከግማሽ አመት በላይ Bridging the Gap የትራንስፖርት ክፍያ ታሪፍ የመንገድ ደህንነት እንዲሻሻል ረድጸዋል፤ መተላለፊያ ኮርደሮቸች ላይ ኢንቨስት ያደረገ ሲሆን ዋና ዋና የእድሳት ሥራዎች ሠርቷል፡፡ የአሁኑ የክፍያ ታሪፍ በ2015 መጨረሻ ላይ ያበቃል፡፡

በመጋቢት 2015 እ.ኤ.አ ከንቲባ Murray የተተኪውን ታሪፍ ረቂቅ ፕሮፖዛል አውጀዋል - ይህ የሲያትል የትራንስፖርት ክፍያ ታሪፍ መሠረታዊ ሃሳቦችን ያገናዘበ እና የበለጠ የሰው እና የእቃ ብዛት እያደገ ባለው በ Seattle እና በዙሪያው ለማጓጓዝ በሚደረጉ ማሻሻዎች ላይ ወደ ፊት ኢንቨስት የሚያደርግ ታሪፍ ነው፡፡

በ March እና በ April ወራት ከንቲባው እና SDOT በረቂቅ ፕሮፖዛሉ ላይ አስተያየት ለማሰባሰብ በ Seattle ውስጥ ያሉ ኮሚኒቲዎችን ወይም ማህበረሰብ አነጋግረዋል፡፡ ማበረሰቡ ለሰጠው ግበረመልስ ምላሽ ለመስጠት ፕሮፖዛሉን ለ Seattle ከተማ ምክር ቤት በግንቦት ወር ውስጥ ከማቅረባችን በፊት ያሻሻልነው ሲሆን በ June 29 የክፍያ ታሪፉን ተግባራዊ ለማድረግ በ November 2015 ምርጫ ድምጽ ይሰጥበታል፡፡

### ወጪ

የ930 ሚሊዮን ዶላር ግብር በቤት ላይ በሚከፈል ግብር አማካይነት የሚከፈል ሲሆን አንድ በሲያትል ያለ የአማካይ ቤት (ዋጋው 450,000 ዶላር የሆነ) ባለቤት በአመት 275 ዶላር ይከፍላል፡፡ በአንፃራዊነት ጊዜው እያበቃ ያለው የ Bridging the Gap የግብር ክፍያ ይህንኑን የቤት ባለቤት በአመት ወደ 130 ዶላር እንዲከፍል ያደርገዋል፡፡

በግብሩ ክፍያ ወቅት ከሚሰበሰበው 930 ሚሊዮን ዶላር በተጨማሪ የ Seattle ከተማ እነዚህ ፈንዶች የ2 ቢሊዮን ተጨማሪ የትራንስፖርት ኢንቨስትመንቶችን ለመቆጣጠር ሊውሉ ይችላሉ፡፡

ይህ የመረጃ ሰነድ በሚቀጥሉት 9 ዓመታት ይህንን የሚሰበሰበውን ግብር (ከፀደቀ) እናወጣበታለን ብለን የምናስባቸውን ፕሮጀክቶች እና የፕሮግራም ዘርፎች ዝርዝር የያዘ ነው፡፡ የከተማው ምክር ቤት በየአመቱ በሚመደበው የከተማ በጀት አማካይነት አመታዊ የምደባ መጠኑን ያስቀምጣል፡፡

በምክር ቤቱ የስራ ሂደት አማካይነት እኛ የመጀመሪያውን አራት የግብር ክፍያ ምድቦችን ወደ ሶስት አዲስ ቡድኖች አሻሽለናል፡፡

1. ደህነታቸው የተጠበቁ መንገዶች
2. እድሳት እና ጥገና
3. የመንገድ መጨናነቅ ማስተንፈሻ

የሚከተሉት ገጾች በእነዚህ አዲስ ምድቦች ውስጥ የተካተቱት ፕሮጀክቶችን እና የገንዘብ መጠን ይዘረዝራሉ፡፡

SDOT
Seattle Department of Transportation

| ምድብ | የግብር ኢንቨስትመንት |
|---|---|
| **ደህነታቸው የተጠበቁ መንገዶች**<br>ወደ ትምህርት ቤት የሚያደርሱ፣ የማዳረሻ እና አገናኝ መንገዶች እና ሌሎች መዳረሻዎች ጋር የሚያገናኙ ደህንነታቸው የተጠበቁ እና አመቺ መንገዶችን ማቅረብ | $207M |
| ምንም አይነት አደጋ እንዳይፈጠር የተቀመጠ ራዕይ - ከባድ እና የሞት አደጋ የሚያስከትሉ ግጭቶችን የማስወገድ ፕሮግራሙን ተግባራዊ ማድረግ | $71M |
| • የሴፍቲ ኮሪደሮች፡ ከፍተኛ አደጋዎች በሚደርሱባቸው መንገዶቻችን ላይ ለሁሉም ተጓዦች የመንገድ ደህንነትን የሚያሻሽሉ ከ12-15 የሚደርሱ የኮሪደር ሴፍቲ ፕሮጀክቶችን ማሟላት | $23M |
| • ወደ ትምህርት ቤት የሚወስዱ ደህንነታቸው የተጠበቁ መንገዶች፡ በየአመቱ ወደ ትምህርት ቤት የሚወስዱ ከ9-12 የሚደርሱ ደህንነታቸው የተጠበቁ መንገድ ፕሮጀክቶችን እና የሴፍቲ ወይም ደህንነት ትምህርት ጋር አሟልቶ ማቅረብ፤ የእግር ጉዞ እና የብስክሌት አነዳድ ሴፍቲን በ Seattle ውስጥ በሚገኙ እያንዳንዱ የሕዝብ ትምህርት ቤት ተግባራዊ ማድረግ፤ ድህነት በከፍተኛ ደረጃ በተንሰራፋባቸው በሚከተሉት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አካባቢ ባሉ የእግር መረማመጃ ዞኖች ላይ የግብር ክፍያው ዘመን የመጀመሪያዎቹ 3 ዓመታት ውስጥ ፕሮጀክቶችን ማጠናቀቅ፡ Bailey Gatzert, Martin Luther King, Jr., West Seattle, Dunlap, Dearborn Park, Wing Luke, Northgate, Van Asselt, Emerson, Concord, Rainier View, Roxhill | $7M |
| • ምልክቶች፡ እያንዳንዱ ዜብራ የመሻገሪያ መንገድ በግልጽ በሚታይ መልኩ ምልክት መደረጉን ለማረጋገጥ የዜብራ መንገዱን ቀለም ለአራት አመት ወይም ከዚያ በላይ ለሆነ ጊዜ እንዲያገለግል አድርጎ በድጋሚ ቀለም መቀባት | $4M |
| • የትራንስፖርት ስራዎች፡ የከተማዋን የትራፊክ መብራቶች እና ምልክቶች ስርዓት ማደስ እና ማሻሻል | $37M |
| የእግረኞች እና የብስክሌት አሽከርካሪዎች ደህንነት - አብዛኛው ለአደጋ ተጋላጭ የሆኑ ተጓዦቻችንን ከአደጋ መጠበቅ - በእግር ለሚራመዱ እና ብስክሌት ለሚነዱ ሰዎች | $110M |
| • የብስክሌት አሽከርካሪዎች ደህንነት፡ በከተማው ውስጥ ያለውን የብስክሌት ማስተር ፕላን ኔትዎርክ ከግማሽ በላይ በማጠናቀቅ በግምት 50 ማይልስ አዲስ የብስክሌት ማሽከርከሪያ መንገድ እና 60 ማይልስ በአረንጓዴ የተሸፈነ መንገድ መገንባት፡፡ በዚህ ምድብ ከተለዩት ፈንዶች መካከል 2 ሚሊዮን ዶላር እንደተደረሸ Mount Baker ፕሮጀክት አካል የብስክሌት መንገድ ማሻሻያዎችን ተግባራዊ ለማድረግ ይያዛል፡፡ | $65M |
| • የእግረኞች ደህንነት፡ በእኛ የከተማ ማዕከላት እና መንደሮች ውስጥ ያሉ እስከ የተጎዱ 225 ብሎክ የመንገድ ዳር መረማመጃ መንገዶች መጠገን | $15M |
| • የእግረኞች ደህንነት፡ በመላ ከተማው እስከ 750 መስቀለኛ መንገዶች ላይ የድንጋይ ጥርብ ከብ መንገዶችን እና የዜብራ መሻገሪያዎች ላይ ማሻሻያዎችን ማድረግ | $30M |
| የጎረቤት ፕሮጀክቶች | $26M |
| • የጎረቤት ፕሮጀክቶች፡ በእነዚህ የጎረቤት ከተሞች ደህንነት፣ እንቅስቃሴን፣ ተደራሽነት እና ጥራትን ለማሻሻል ከ20-35 የጎረቤት ቅድሚያ የሚሰጣቸው ፕሮጀክቶችን ማጠናቀቅ | $26M |
| **እድሳት እና ጥገና**<br>ዋና ዋና አውራ ጎዳናዎች እና የ Seattle እጅግ የሚጨናነቁ መንገዶች የእድሳት እና የጥገና ስራ መጓተትን መቀነስ | $420M |
| መንገዶችን ማደስ | $250M |
| • የአውራ ጎዳና እድሳት፡ እስከ 180 ማይልስ አውራ ጎዳናዎችን በድጋሚ ማንጠፍ፣ 35 በመቶ የ Seattle እጅግ በጣም የሚጨናነቁ እና አብዛኛውን ነዋሪዎች እና እቃዎችን የሚያጓጉዙ መንገዶችን ማደስ እና ዘመናዊ ማድረግ (ከዚህ በታች በተዘረዘሩት 7 ከፍተኛ የመተላለፊያ ኮሊደሮች በኩል ፈንድ ተይዞለታል) | $235M |
| • በአስፓልት የተሸፈነ መንገድ ማሻሻያዎች፡ በየአመቱ 65 የተመረጡ ቦታዎችን በድጋሚ በአስፓልት መሸፈን ሲሆን ጠቅላላው ወደ 70 ማይልስ የሚደርሱ እጅግ በጣም የሚጨናነቅ መንገድ ሲሆን ይህን በከተማው ሰራተኞች በሚሰራ የእድሳት እና የጥገና ፕሮግራም አማካይነት ማከናወን | $15M |

| | |
|---|---|
| ድልድዮች እና ስትራክቸሮች - ድልድዮቻችን ደህንነታቸውን እንጠብቃለን | $140M |
| • የድልድዮች እና የስትራክቸሮች እድሳት - በተጎዱ ድልድዮች ላይ የሚደረገውን ጥገና የማጓተት ተግባር ማስወገድ | $25M |
| • የድልድይን የመሸከም አቅም ወይም ጥንካሬ ማሻሻል፡ 16 የሚደርሱ ተጋላጭ ድልድዮችን የመርገብገብ ጉዳትን መቋቋም በሚችል መልኩ መገንባት ወይም ማጠናከር | $68M |
| • ምትክ ድልድይ፡ (በ Fairview Avenue ላይ ያለውን) የ Seattle የመጨረሻው የጣውላ የመኪና ድልድይ መተካት | $27M |
| • ምትክ ድልድይ፡ ከ2024 በኋላ ግንባታ ለመጀመር በከፍተኛ ደረጃ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ምትክ ድልድዮችን ማቀድ እና ዲዛይን ማድረግ፤ በዚህ ምድብ ከተለዩት ፈንዶች መካከል ከጠቅላላ ፈንዱ (የሀገር ውስጥ፣ ቀረጥ፣ የገቢ ማሳደጊያ) ውስጥ እስከ 10 ሚሊዮን የሚደርሰው የቅርብ አመት የእግረኛ እና የብስክሌት ደህንነት ፕሮጀክቶችን ለመተካት በተጠኑ ድልድዮች (በሌሎች ዘርፎች ውስጥ ለእግረኞች እና ለብስክሌት ደህንነት ፕሮጀክቶች የተሰጠ ፈንድ ጨምሮ) ላይ ተፈፃሚ ለማድረግ ጥቅም ላይ ይውላል | $15M |
| • የድልድይ እና የስትራክቸር እድሳት፡ የደረጃዎች እና ስትራክቸር እገዳ እና እድሳት ጨምሮ ሌሎች የድልድይ ደህንነት ኢንቨስትመንቶች | $5M |
| የከተማ ደን እና የፍሳሽ ማስወገጃ | $30M |
| • ዛፍ መከርከም፡ ዛፍ የመከርከም አንገብጋቢ ፍላጎት (ብስክሌት ለሚነዱ እና በእግር ለሚራመዱ ሰዎች ክፍተት መፍጠር እና ለጊዜያዊ መሸጋገሪያ የሚሆኑ ማቆሚያ ቦታዎች የመሳሰሉ) በተመለከተ አፋጣኝ ምላሽ ለመስጠት እና የትራፊክ ምልክቶች መብራቶች በግልጽ ቦታ ላይ ሆነው የሚታዩ መሆናቸውን ለማረጋገጥ አዲስ የዛፍ ከርካሚ ሰራተኛን መጨመር<br>• ዛፍ መትከል፡ በበሽታ ወይም በደህንነት ምክንያት የተወገደውን እያንዳንዱ ዛፍ በሁለት አዲስ ዛፎች መተካት | $20M |
| • የፍሳሽ አወጋገድ አጋርነት፡ የመንገድ አስፓልት ለማንጠፍ፣ ለእግረኞች አዳዲስ መሰረተ ልማቶችን እና መሻገሪያ መንገዶችን ለማቅረብ እና በ South Park መንደር ያለውን የጎርፍ ፍሳሾችን የማስወገድ ችግር ይፋ ለማድረግ ከ Seattle Public Utilities ጋር በትብብር መስራት | $10M |
| የመንገድ መጨናነቅ ማስተንፈሻ<br>በመላው ኔትወርኩ የትራንስፖርት አማራጮችን ማሳደግ | $303M |
| የኮሪደር እንቅስቃሴ ማሻሻያዎች- መንገዶችን ዘመናዊ ማድረግ | $169M |
| • መልቲሞዳል ማሻሻያዎች - በእግር፣ በብስክሌት፣ በመኪና ወይም ለመተላለፊያ የሚሄዱ ሁሉም ተጓዦች የተደራሽነት እና የደህንነት ሂደቱን ለማሻሻል አብዛኛውን ጊዜ ብዙ አውቶቡሶች በአስተማማኝ ሁኔታ የሚጓዙባቸው ዋና ዋና መንገዶችን፣ ደረጃቸው ከፍ ያሉ የአስፓልት ንጣፎችን፣ የመንገድ መብራቶችን እና ሌሎች ማሻሻያዎችን በድጋሚ ዲዛይን ማድረግ፤ የ Burke Gilman ወጥነት የሌለው መንገድ፣ Fauntleroy Way Southwest Boulevard ፕሮጀክቶች ማጠናቀቅ፣ በ4th Ave NE እና በ Brooklyn Ave NE መካከል ያለውን NE 45th St ኮሪደር በ2021 የ University ቀላል ባቡር መንገድ ሲከፈት ለእግረኞች እና በብስክሌት ተጓዦች ተሻሽሎ ለ Aurora Ave N እንዲቀርብ ማድረግ | $104M |
| • የትራፊክ መብራቶች የሰዓት ማሻሻያዎች፡ በከተማዋ ውስጥ በየአመቱ በ5 ኮሪደሮች ላይ የትራፊክ መብራቶችን ሰዓት ለማሻሻል የትራፊክ ፍሰቱን ማሻሻል እና በመኪና እና በከባድ መኪኖች፣ በብስክሌቶች፣ ለመተላለፊያ የመጡትን እና በእግር የሚጓዙትን ሰዎች ማገልገል | $13M |
| • እጅግ በጣም ጥሩ የትራንስፖርት ስርዓት ማሻሻያዎች፡ ሁሉም ተጓዦች የበለጠ አስተማማኝ በሆነ መንገድ በከተማ ዙሪያ መንቀሳቀስ እንዲችሉ ለቀጣይ ትውልድ የሚሆን እጅግ በጣም ጥሩ የትራንስፖርት ስርዓት ማሻሻያዎች ተግባራዊ ማድረግ | $17M |
| • የመተላለፊያ ኮሪደር ማሻሻያዎች፡ በቁልፍ ቦታዎች ላይ የሚታዩትን እንቅፋቶች ለማስወገድ እና West Seattle ባህረሰላጤ ላይ የሚደረጉ የተደራሽ መንገዶች ማሻሻያ እቅድ ጨምሮ በ7 የመተላለፊያ ኮሪደሮች ላይ የሚደረጉ የትራንዚት ማሻሻያዎች አስተዋጽኦ ለማድረግ በአጠቃላይ የትራንዚት ማሻሻያ ፕሮግራም አማካይነት የአውቶቡስ አገልግሎትን የበለጠ አስተማማኝ ማድረግ | $35M |

| | |
|---|---|
| የቀላል ባቡር አጋርነት ማሻሻያዎች - ከቀላል ባቡር ከመንገዶች ጋር የሚያገናኙ መስመሮችን | $27M |
| • ማሻሻል፡ በደቡብ ምስራቅ Seattle ውስጥ በሚገኘው የ Graham Street ለአዲሱ ለቀላል ባቡር መንገድ ጣቢያዎች የከተማ ፈንድ አስተዋጽኦ ማድረግ | $10M |
| • Northgate ድልድይ፡ በ Northgate ከI-5 የሚደርሱ መስመሮችን ከቀላል ባቡር ጋር በማገናኘት ለእግረኞች እና ለብስክሌተኞች የሚያገለግል ድልድይ ለመስራት ተጨማሪ የከተማ ፈንድ ማቅረብ | $15M |
| • የቀላል ባቡር መስመር ግንኙነቶች፡ የተደራሽ Mt. Baker ፕሮጀክት የመጀመሪያዎቹን ክፍሎች ተግባራዊ ማድረግ | $2M |
| የእግረኞች እና የብስክሌት መንገዶችን ማሻሻል - በእግር ለሚራመዱ እግረኞች እና ብስክሌተኞች መንገዶችን ቀላል ማድረግ። በዚህ ምድብ ከተለዩት ፈንዶች መካከል 2 ሚሊዮን ዶላር የተደራሽ Mount Baker ፕሮጀክት አካል የሆነውን የእግረኛ መንገዶች ማሻሻያ ተግባራዊ ለማድረግ ይያዛል፡፡ | $68M |
| • አዲስ የመንገድ ዳር መረማመጃ መንገዶች፡ በመላ የከተማው ክፍል ባሉ ቅድሚያ የሚሰጣቸው የትራንዚት መተላለፊያ ኮሪደሮች ላይ ባሉ የመንገድ ዳር መረማመጃ ክፍተቶችን 75 በመቶ በላይ ለማሟላት 150 ብሎክ አዳዲስ የመንገድ ዳር መረማመጃዎችን መገንባት እና በዚህ ጊዜ ለአካል ጉዳቶኞች እና ለአዛውንቶች ተደራሽ የሆኑ መንገዶችን በመፍጠር ላይ ትኩረት ማድረግ<br>• የብስክሌት እና የእግር ጉዞ ፋሲሊቲዎች፡ የመንገድ ዳር መረማመጃዎች የሌላቸው የመኖሪያ አካባቢ መንገዶችን ከ Seattle Public Utilities ጋር በመተባበር በ Broadview ያለውን አካባቢ የጐርፍ ማውረጃ ውስጥ ያለውን ጨምሮ ለሎች አካቢዎችን የበለጠ ደህንነታቸው የተጠበቀ ማድረግ | $61M |
| • የብስክሌት እና የእግር ጉዞ ፋስሊቲዎች፡ 1,500 አዳዲስ የብስክሌት ማቆሚያ ቦታዎችን በመላ ከተማው መትከል እና ያሉትን የብስክሌት ፋሲሊቲዎች ማደስ<br>• የብስክሌት እና የእግር ጉዞ ፋስሊቲዎች፡ ሌሎች የብስክሌት እና የእግር ጉዞ ኢንቨስትመንቶችን ማከናወን | $7M |
| የጭነት እንቅስቃሴ መንገዶች ማሻሻያ - ጭነት እና ርክክብ | $39M |
| • የአጋርነት ማሻሻያ፡ የ Lander Street የላይኛውን መተላለፊያ ዲዛይን ለማድረግ እና ለመገንባት ገንዘብ ማቅረብ | $20M |
| • የከባድ መኪኖች ኔትዎርክ፡ በሲያትል የከባድ መኪዎች ኔትዎርክ ውስጥ ቁልፍ መንገድ የሆነውን የ East Marginal Way ኮሪደር መገንባት | $5M |
| • የማቆሚያ ቦታዎች ማሻሻያ፡ የጭነት እንቅስቃሴውን ለማገዝ የተመረጠ የማቆሚያ ቦታዎች ማሻሻያ ለማሰራት ፈንድ ማድረግ | $14M |
| ጠቅለላ ድምር (በሁሉም ምድቦች) | $930M |

የበለጠ መረጃ ለማግኘት www.seattle.gov/LevytoMoveSeattle

---

ጥያቄዎች ካልዎት ALLISON SCHWARTZ በ ALLISON.SCHWARTZ@SEATTLE.GOV ወይም (206) 386-4654 ያግኙ